…………………………………………………………………… 14
3.1.3 በክልል፣ በወረዳና በት/ቤት (ጣቢያ) ደረጃ የትምህርት ዕቅድና 15
አመራርን ማሻሻል 15
…………………………………………………………………… 16
3.2 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት 16
…………………………………………………………………… 16
3.3 የርቀት ትምህርት 17
…………………………………………………………………… 17
3.4 የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና
……………………………………………………
3.5 መደበኛ ያልሆነ የጎልማሶች ትምህርት
……………………………………..
3.6 የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ማስቀረት
…………………………………………
3.7 የሬዲዮ ትምህርትን በስፋት መጠቀም
…………………………………………
3.8 በየደረጃው ላሉ መምህራንና ባለሙያዎች ልዩ የማትጊያ ስልት መንደፍ.
3.9 ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ
……………………………………………………….
3.10 ትስስርና አጋርነት……………………………………………………………………
3.11 የአስፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት
…………………………………………

## 1. መግቢያ

ትምህርትን ለሁሉም ዜጋ የማዳረስ ተግባር በአሁኑ ጊዜ ዓለምአቀፋዊ ጉዳይ ብሎም ብሔራዊ አጀንዳ ሆኖአል። ማንኛውም ግለሰብ እድሜ፣ ፆታ፣ ሃይማኖትና የቀለም መድልኦ ሳይደረግበት የመማር መብት ያለው ስለመሆኑ በተባበሩት መንግሥታት

የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ውስጥ ሰፍሯል። ይህም እውነታ በአገራችን ህገ መንግሥት ውስጥ በማያሻማ መልኩ ተቀምጧል።

ከዚህ በመነሳት ለዘመናት በአገራችን ሥር ሰደው የቆዩትን የትምህርት ስርጭት ጥራት፣ ተገቢነትና ፍትሃዊነት ችግሮች በመቅረፍ ትምህርትን በስፋትና በጥራት ለሁሉም ለማዳረስ የሚያስችል የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ወጥቶ በሁሉም የትምህርት ተቋማት በመተግበር ላይ ይገኛል። በዚሁ ሰነድ ትምህርትን የችግር ፈቺነትን አቅምና ባህል ለማጎልበት እንዲያስችል ሳይንሳዊና በተግባር ሊተረጎም የሚችል ማድረግና አመቺ የትምህርት አካባቢ መፍጠር ተገቢ መሆኑ ተጠቅሷል። በተለይ ትምህርት ተነፍገው ለቆዩ አካባቢዎች መንግሥት የተለየ እገዛ እንደሚሰጥና የሴት ተማሪዎች ተሣትፎ እንዲጨምር ማበረታቻዎች እንደሚያደረግ በፖሊሲው ተገልጿል። /1986 አዲሱ የትምህርት ሥልጠና ፖሊሲ/

ተገቢነት ያለውን ትምህርት በስፋትና በጥራት ለማዳረስ፣ እንዲሁም የሥርጭቱን ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ ከላይ የተጠቀሱት ምቹ የፖሊሲ ሁኔታዎች ቢኖሩም በአርብቶአደር አከባቢዎች የሚጠበቀውን ያህል እድገት አልታየም።

የአርብቶአደር አካባቢዎች ለዘመናት ተረስተው የቆዩና መሠረታዊ የልማት አውታሮች ያልተስፋፉባቸው በመሆኑ ልማትም ሆነ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች የሚፈለገውን ያህል አልተስፋፉባቸውም በተለያዩ ጥናቶች እንደተረጋገጠው ችግሮቹ በአርብቶአደር አካባቢዎች ካሉ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መልክአ-ምድራዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ሲሆኑ ድርቅ፣ ድህነት፣ የት/ቤት ርቀት፣ ጎጂ ልማዶች እና የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የትምህርት ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ በተለይም በሶስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ለአርብቶአደር ትምህርት ልዩ ትኩረት በመሰጠቱ በሁሉም የትምህርት ዘርፎች Mainstream በመደረግ ላይ ይገኛል።

ለአርብቶ አደሩ ትምህርት ልማት ምቹ ሁኔታ በመፈጠሩ የትምህርት ተሳትፎው ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕድገት እያሳየ የመጣ ቢሆንም የዕድገቱ መጠን ከሚፈለገውና በአገር አቀፍ ደረጃ ከተመዘገበው ዕድገት ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛ ነው። ለምሳሌ በ1998ዓ.ም

የመጀመሪያ ደረጃ ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ የአገር አቀፍ አማካይ የተሳትፎ መጠን 91.3% (ወ. 98.% ሴ. 83.9%) ሲሆን፣ በአፋር 21.9% (ወ. 24.2% ሴ. 19.1%) በሶማሌ 30.3% (ወ. 35.4% ሴ. 24.4%) ብቻ ነው። ይህ ሁኔታ በትምህርት ዘርፍ የሚታዩ አበይት ችግሮችን ለይቶ የሚታየውን ክፍተት ለመሸፈን የሁሉንም አካላት ርብርብና ልዩ ልዩ ስልቶችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ አመላካች ነው። በመሆኑም በአርብቶ አደሩ አካባቢዎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በስፋትና በጥራት በማዳረስ ፍትሃዊ የትምህርት ስርጭት የሚያሰፍን ስልት መንደፍ ወቅታዊ ጉዳይ በመሆኑ ይህን ሰነድ ማዘጋጀት አስፈልጓል።

## 2. በአርብቶ አደሩ አካባቢ ትምህርትን በጥራት ለማዳረስ ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎችና ያጋጠሙ ችግሮች፣

### 2.1 ተስፋ ሰጭ ሁኔታዎች

- ያልተማከለ የአስተዳደርና የትምህርት ስርዓት በወረዳ ደረጃ ተግባራዊ መደረጉ የቢሮክራሲ ውጣ ውረድ መቀነሱ ለአፋጣኝ ውሳኔ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ፣ በመንግሥትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በሚካሄዱ ፕሮጀክቶች መካከል የነበረ ክፍተት እጠበበ መሄዱ፣በህብረተሰቡ ዘንድ የባለቤትነት ስሜትና ተሳትፎ ማሳደጉ፣
- በፌደራል መንግሥት ደረጃ ለአጠቃላይ ልማትና ማሕበራዊ እድገት የሚረዱ ምቹ የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች መነደፋቸው፣ ከዚያም ባሻገር ለአርብቶ አደሩ ክልሎች ልዩ እገዛ ለማድረግ የፌደራል የልዩ ዕገዛ ቦርድ ተቋቁሞ የቴክኒክ ኮሚቴ በማደራጀት ከክልሎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በማደረግ እንቅስቃሴ መጀመሩና ትምህርት ሚኒስቴርም የዚህ እንቅስቃሴ አካል መሆኑና የአርብቶአደሩን ትምህርት የሚከታተል አካል መኖሩ። አጎራባች ክልሎችም ድጋፍ ለማድረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመራቸው፣ ከሁሉም በላይ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት የአርብቶ አደር ክልሎች የራሳቸው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ መንደፋቸውና በትምህርት ዘርፍም የእስትራቴጂ ዕቅድ ማዘጋጀታቸው፣ ከዚህም በተጨማሪ ዓለም አቀፍና አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአርብቶአደር ትምህርት ሥራ ላይ ከመንግሥት ጐን እንዲሰለፉ የሚያበረታታ

ምቹ የፖሊሲ አቅጣጫ መኖሩ ለትምህርቱ ዘርፍ ዕድገት የተሻለ ሁኔታ መኖሩን ያመለክታል።

## 2.2 ያጋጠሙ ችግሮች

በፌደራልና የአርብቶ አደር ክልል መንግሥታትና እንዲሁም ሕብረተሰቡ ያለውን አቅም አስተባብሮ ትምህርትን በአርብቶ አደሩ አካባቢ በጥራት ለማስፋፋት የጎላ እንቅስቃሴ እየተደረገ ቢሆንም መሰራት ካለበት አንፃር ሲታይ ብዙ እንደሚቀር የተለያዩ አገራዊና ክልላዊ ጥናቶች ያመለክታሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከክልሎቹ ትምህርት ባለሙያዎችና አመራር አካላት ጋር በተደረጉ የምክክር ጉባኤዎች ላይ ከጋራ መግባባት ላይ ከተደረሰባቸው የትምህርት ሥርጭትና ጥራት ችግሮች መካከል የሚከተሉትን በአብነት መጥቀስ ይቻላል።

### 2.2.1 ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች

- የአርብቶ አደሩ ክልሎች ባለፉት መንግሥታት ከሌሎች አካባቢዎች በባሰ መልኩ ከልማት እንቅስቃሴዎች ተዘንግተው የቆዩ መሆናቸው፣
- የአርብቶ አደሩ ኑሮ በአብዛኛው ኋላቀር በሆነ የከብት እርባታ ምጣኔ ሀብተ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ሕብረተሰቡ የትምህርት ሥርዓቱን በገንዘብና ማቴሪያል ለመደገፍ ያለው አቅም ውስን መሆኑ፤
- በአርብቶ አደሩ ገጠር አካባቢዎች የሕብረተሰቡ አኗኗር ተንቀሳቃሽና በከፊል ተንቀሳቃሽ መሆኑና ቋሚ ሰፋሪውም ቢሆን በተበታተነ ሁኔታ መኖሩ መሠረታዊ የልማት አውታሮችን /ውሃ፣ ጤና፣ መንገድ ወዘተ/ በበቂ ሁኔታ ለማስፋፋት አስቸጋሪ መሆኑ በዚህም ምክንያት፣
  - ትምህርት ቤቶችን ሕብረተሰቡ በሚኖርባቸው መንደሮች በሙሉ ማቋቋም አለመቻሉና፣
  - ለሴቶችና ሕፃናት ትምህርት ማቋረጥ ዋነኛ ምክንያት መሆኑ፤
- ፍትሃዊ የትምህርት ሥርጭት በአርብቶ አደር ክልሎች በወንዶችና በሴቶች፣ ከወረዳ ወረዳና በከተማና ገጠር መካከል አለመኖር፤
- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ኋላ ቀር አኗኗርና አስተሳሰብ ሥር የሰደዱ በመሆናቸው፣
  - ለትምህርት ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን፤
  - ሴት ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት አለመላክ፤

- ጎጂ የሆኑ ልማዳዊ ድርጊቶችና አስተሳሰቦች በሕብረተሰቡ ዘንድ ሥር የሰደዱ ችግሮች መሆናቸው፤
- አልፎ አልፎ በአርብቶ አደሩ አካባቢ በግጦሽና በውሀ እጥረት ምክንያት የሚከሰቱ መለስተኛ ግጭቶች ለቤተሰብ መፈናቀልና ለተማሪዎች ትምህርት ማቋረጥ ምክንያት መሆናቸው፣

- በአርብቶ አደሩ አካባቢ በየወቅቱ የዝናብ እጥረትና ተደጋጋሚ ድርቅ መከሰቱና በተለይም የባሰ ችግር ባለባቸው አንዳንድ አካባቢዎች የትምህርት ቤት ምገባ ኘሮግራም አለመኖር ይህም ለተማሪዎች ትምህርት ማቋረጥ ዋነኛ ምክንያት መሆኑ፣
- የልጆች ጉልበት በቤተሰብ ለልዩ ልዩ ተግባራት መፈለጉ፤

## 2.2.2 የሰለጠነ ሰው ሃይል ችግር

- በአርብቶ አደር ክልሎች በተለያዩ ደረጃዎች የትምህርቱን ሥራ በተቀላጠፈ መንገድ እንዲመሩ የሚቀመጡ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች በአብዛኛው የአቅም ብቃት ችግር ያለባቸው መሆኑና ከዚህም በላይ ሃላፊዎቹ በየወቅቱ በፍጥነት መቀያየራቸው፤
- በክልል በወረዳና በትምህርት ቤት ደረጃ በአስፈጻሚነት የሚመደቡ ባለሙያዎችን በበቂ መጠን አለማግኘትና ያሉትም ባለሙያዎች ያላቸው የማስፈፀም አቅም ውሰን መሆኑ፣
- ውስን የሆነውን የክልል ሀብት ልማት ተግባር አግባቡ ሥራ ላይ አለማዋል፣
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ተሳትፎን በማሳደግ በጐ አስተዋጽኦ ቢኖረውም በክልልና ወረዳ ደረጃ ያሉ የትምህርት አመራሮችና ባለሙያዎች ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የመደበኛውን ትምህርት ያህል ትኩረት አለመስጠታቸው፣
- የሱፐርቪዥን የዕቅድ ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ደካማ መሆን፣ በሥራው ላይ ያሉ ባለሙያዎችም በቂ ሥልጠና ያልውሰዱ መሆናቸው፣
- በመማር ማስተማሩ ሂደት ግንባር ቀደም የሆኑ መምህራንን በበቂ ቁጥር አለማግኘትና በሥራ ላይ ያሉትም ቢሆኑ ለሙያው ያላቸው ፍቅርና ተነሳሽነት የተፈለገውን ያህል አለመሆን፤
- በአርብቶ አደሩ አካባቢ በቂ ባለሙያዎችን ለመቅጠርና ሥራ ላይ ለማቆየት ልዩ ማበረታቻ ያለመኖሩ፣

### 2.2.3 የአመራሩ ቁርጠኝነት የሚፈለገውን ያህል አለመሆን

- በክልልና ወረዳ ደረጃ ያሉ አመራር አካላት ለትምህርቱ ሥራ የሚፈለገውን ያህል ትኩረት አለመስጠታቸው ለምሣሌ ያህል ለትምህርቱ ዘርፍ በቂ በጀት አለመመደቡ፣ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አመቻቾች ደመወዝ ወቅቱን ጠብቆ አለመከፈሉ፣ በትምህርቱ ዘርፍ በበቂ ክትትልና ግምገማ ላይ የተመሰረቱ የማስተካከያ እርምጃዎች ያለመወሰዳቸው፣
- የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ለአርብቶ አደር ክልሎች ልዩ ልዩ ድጋፎችን ሲሰጥ የቆየ ቢሆንም ከ1999.ዓም. በፊት የነበሩ ድጋፎች የሚፈለገውን ያህል የተቀናጁና በጋራ ያልታቀዱ የነበሩ መሆናቸው፤ አሁንም ቢሆን የሚፈለገውን ያህል የተጠናከሩ አለመሆናቸው።
- በየደረጃው ያለ አመራር ለትምህርት ሥራ ሕብረተሰቡን ሞብላይዝ የማድረግ አቅሙ ውስን መሆኑ፣
- በትምህርት ሥራ ሴቶች በአመራር ደረጃ ያላቸው ቦታ እጅግ ውስን መሆኑ፣

### 2.2.4 የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ችግሮች

- የአርብቶ አደሩን አኗኗር ግምት ውስጥ ያስገቡ የተለያዩ የትምህርት አቅርቦት ሥልቶች አለመኖር፤
- ለአርብቶ አደሩ የሚዘጋጁ ሥርዓተ ትምህርቶች የሕብረተሰቡን ባሕል፣ ወግና ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘቡ አለመሆናቸው፣
- ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የሚዘጋጁ የመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት የጥራት ደረጃ ዝቅተኛ መሆን፣
- ቢያንስ የመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል /1-4/ ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ አለመስጠቱ /በተለይ በአፋር ክልል/
- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ባሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተለይም በሶማሌ ክልል ከፍተኛ የሆነ የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሀፍትና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እጥረት መኖሩ።

# 3. በአርብቶ አደሩ አካባቢ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ማሳደጊያ ስልቶች /የትኩረት ነጥቦች/፣

ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች ለመፍታት፣ በአገራችን የተጀመረውን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በአስተማማኝ መሠረት ላይ ለማቆምና ሕብረተሰቡ የልማትና መልካም አስተዳደር ተጠቃሚ እንዲሆን የትምህርት ዘርፍ ልማት አስተዋጽኦ ወሳኝነት አለው። በተለይ በአርብቶ አደሩ ክልሎችና አካባቢዎች ጥራት ያለው ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ለማዳረስ የሕብረተሰቡን ልዩ አኗኗር፣ ሥነምህዳራዊ ሁኔታና ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት ስልት መቀየስ አስፈላጊ ይሆናል። ከዚህ ጋር በተያያዘ መደበኛ በሆነ የትምህርት አቅርቦት ሥልት ብቻ ትምህርትን ለአርብቶ አደሩ ልጆች ማዳረስ እንደማይቻል ካለፈው ተሞክሮአችን በመማር አማራጭ የትምህርት መሰጫ መንገዶችን ሁሉ በመጠቀም የክልሎቹን የትምህርት ተሳትፎ በፍታዊነት ማሳደግና የትምህርት ለሁሉምና የምዕተ ዓመቱ ግቦችን እውን እንዲሆኑ ማድረግ ወቅታዊ ጉዳይ ነው። ስለሆነም ይህን የአርብቶ አደር ትምህርት የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለማሳደግ የሚረዳ ስልት ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል።

### ዓላማ

- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ጥራትና ተገቢነት ያለው ትምህርትን በስፋትና በፍትሃዊነት ህብረተሰቡን አሳታፊ በሆነ መልኩ ማዳረስ፣
- በአርብቶ አደር ክልሎችና በሌሎች ክልሎች መካከል ያለውን ሰፊ የትምህርት ተሳትፎ ልዩነት ማቀራረብ፤

## 3.1 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት

### 3.1.1 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አቅርቦትን ማስፋፋት

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በአርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚገኙ ሕፃናት ለማዳረስ የሚከተሉት ስልቶች ተቀይሰዋል፡፡

#### 3.1.1.1 የተለያዩ አማራጭ የትምህርት አቅርቦት ዘዴዎችን መጠቀም

ሀ. አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት

- አርብቶ አደሩ በአንድ ዓመት ውስጥ ቢያንስ ለ8 ተከታታይ ወራት በሚኖርባቸው አካባቢዎች ወጪ ቆጣቢ የሆኑ ቋሚ የመንደር ትም/ቤቶችን (ጣቢያዎች) ሕብረተሰቡን በማሳተፍ ማቋቋም፡፡ የትምህርት ፕሮግራሙ የህበረተሰቡን፣ የተማሪውንና የመምህሩን ፍላጎት ያካተተ ተለማጭና/flexible/ እና child friendly እንዲሆን ማዳረግ፣
- በአርብቶ አደር አካባቢዎች በስፋት (በመንደር ደረጃ) የሚገኙትን የቁርዓን ት/ቤቶች
  - በማህበረሰቡና በሀይማኖት መሪዎች ፈቃድ የቁርዓን ትምህርት በማይሰጡበት ጊዜ በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ማዕከልነት መጠቀም፣
  - በእነዚህ ተቋማት የሚሰጠው አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዓላማዊ (secular) መሆኑን ማረጋገጥ
- ከመደበኛው ሥርዓተ ትምህርት ጋር አቻነት ያለውና ከየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተዛማጅነት ያለው የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት መቅረጽ፣
- በአካባቢው ከሚገኙ የሰው ሀይል የተሻለ የትምህርት ደረጃ ያላቸውን በአመቻችነት መመልመል፣ በምልመላው ወቅት ለሴቶች ቅድሚያ መስጠት፣ በአመቻችነት ለተመለመሉ የቅድመ ሥራና የሥራ ላይ ሥልጠና ማዘጋጀት፣
- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን የትምህርት ሥርዓቱ አካል ማድረግ፣ በክልል ደረጃ የትምህርት ፕሮግራሞችና ስትርቪዥን መምሪያ በባለቤትነት እንዲመራውና እንዲያስተባብረው ማድረግና የቢሮ ሀላፊው የቅርብ ክትትልና እገዛ እንዲያደርግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

www.chilot.me

ለ. ተንቀሳቃሽ ትምህርት

- ሕብረተሰቡ በአንድ ዓመት ውስጥ ከአራት ወር በላይ ከቦታ ቦታ በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች ተንቀሳቃሽ የትምህርት አቅርቦት ዘዴን /ድንኳን፤ ተጣጣፊ ሰሌዳ፣ ምንጣፍ ወዘተ/ በመጠቀም አማራጭ የመሠረታዊ ትምህርት አገልግሎት መስጠት፣
- የተንቀሳቃሽ ትምህርት አገልግሎት መስጠት ለመጀመር በቅድሚያ የሕብረተሰቡን እንቅስቃሴ ሁኔታ፣ ሕብረተሰቡ በጊዜያዊ መጠለያነት የሚሰባሰብባቸውን ሥፍራዎች ወዘተ መለየት፣
- ሕብረተሰቡ በታወቁ አካባቢዎች ለአጭር ጊዜ ቆይታ በሚያደርግባቸው ቦታዎች በቋሚ መንደር የሚሰጠውን ትምህርት የሚደግፍ ጊዜያዊ የትምህርት መስጫ ጣቢያ በማቋቋም የከፊል ተንቀሳቃሽ ትምህርት አገልግሎት መስጠት፣

ሐ. መደበኛ ያልሆኑ አዳሪ ትምህርት ቤቶች (Para-boarding schools)

- ከአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ የአኗኗር ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ፣ ከአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ የሚገነቡ፣ ማህበረሰቡ በግንባታ ሥራ ውስጥ በማቴሪያል አቅርቦትና በጉልበት አስተዋጽኦ የሚያደርግባቸውና ተቋማቱን በባለቤትነት በማስተዳደር የሚሳተፍባቸው መደበኛ ያልሆኑ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን እንደአስፈላጊነቱ ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል /5-8 ክፍል/ተማሪዎች ማቋቋም። የቦታ እጥረት ሲያጋጥም ቅድሚያ ለሴቶች መስጠት፣
- መደበኛ ያልሆኑ አዳሪ ትምህርት ቤቶች በተቻለ መጠን የውስጥ ገቢ የሚያፈሩበትን ስልት በመቀየስ የትምህርት ወጪን እንዲጋሩ ማድረግ፣

መ. የሆስቴል አገልግሎት

- በአካባቢያቸው የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል /5-8/ ትምህርት አገልግሎት ለማያገኙ የአርብቶ አደር ልጆች የትምህርት ተቋማቱ በሚገኙባቸው አካባቢዎች በዝቅተኛ ወጪ መጠለያዎችን በመገንባት የሆስቴል አገልግሎት መስጠት ።

ሠ. መደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች

- ሕብረተሰቡ በቋሚ ሰፈራና በከፍተኛ ቁጥር በሚኖርባቸው አካባቢዎች በአነስተኛ ወጪና በህብረተሰቡ ተሣትፎ መደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችን መገንባት፣
- በነባር የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ መማሪያ ክፍሎችን በመገንባት የአዲስ ተማሪ ቅበላ አቅማቸውን ማሳደግ፣
- የትምህርት መስጫ ጊዜን እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተለማጭ (flexible) በማድረግና ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ት/ቤት እንዲልኩ ተገቢውን ቅስቀሳ በማድረግ ከአቅም በታች የሚሰሩ የመጀመሪ ደረጃ ት/ቤቶችን የተማሪ ቁጥር ማሳደግ፣
- በአርብቶ አደሩ በጣም የተበታተነ አሰፋፈር ምክንያት የተማሪዎች ቁጥር በየክፍል ደረጃው በጣም አነስተኛ በሆነባቸው ትምህርት ቤቶች የMulti grade የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን መጠቀም ለዚህም ተግባራዊነት መምህራን በቂ ሥልጠና እንዲወስዱ ማድረግ፣
- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ያጠናቀቁና በአቅራቢያቸው የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤት ለማያገኙ ተማሪዎች እንደአስፈላጊነቱ በማህበረሰቡ ተሳትፎ ላይ የተመሠረቱ፡
  - ወጭ ቆጣቢ የሆኑ አዳሪ ት/ቤቶችንና ሆስቴሎችን ማቋቋም፣
  - በአካባቢው ከሚገኙ አማራጭ መሠረታዊ ት/ቤቶች መካከል በአማካይ ቦታ ያለውን በመምረጥ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ት/ቤት ማሳደግ፣
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንን በበቂ ቁጥርማሰልጠን፣

### 3.1.1.2 በአርብቶ አደሩ ዘንድ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት

- አርብቶ አደሩ ያታዊ ሚናዎችን፣ የዓለማዊ ትምህርትን (secular education) እና የሴቶችንና ወንዶችን በአንድ ላይ መማር (co-education) ጠቀሜታ፣ ያለዕድሜ ጋብቻንና መሰል ልማዳዊ ድርጊቶችን በሚገባ እንዲገነዘብ ማድረግ፡፡ ይህን እውን ለማድረግም ተከታታይነት ባላቸው ሕዝባዊ ስብሰባዎች፣ አውደጥናቶች፣ የጎልማሶች ትምህርትና ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች አማካኝነት ሰፊ የአህዝቦትና የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥራዎችን ማከናወን፣

- በአርብቶ አደር አካባቢዎች "የትምህርት ለሁሉም"ን ግብ ተግባራዊ ለማድረግ የሕብረተሰቡን አቅም አስተባብሮ ማንቀሳቀስ፣
- ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ግቦች ለማሳካት የፖለቲካ፣ የሀይማኖትና የማህበረሰብ መሪዎችን ወሳኝ ሚና ተገንዝቦ ጥቅም ላይ ማዋል፡፡

### 3.1.1.3 ለተማሪዎች ትምህርት ማቋረጥ ምክንያት የሚሆኑ አካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ

- ንፁህ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት በመደበኛ ት/ቤቶችና በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች እንዲኖር ማድረግ፣
- ሴትና ወንድ ተማሪዎች ለየብቻ የሚገለገሉባቸው መፀዳጃ ቤቶችን ማዘጋጀት፣
- የትምህርት መስጫ አካባቢን ለሕፃናት ምቹ (child-friendly) ማድረግ፣
- በባሰ ድህነት ምክንያት ትምህርታቸውን መከታተል ላቃታቸው ተማሪዎች በተለይም ለሴት ተማሪዎች ልዩ ልዩ ድጋፍ /የጽሕፈት መሣሪያዎችን፣ የመማሪያ መጽሐፍትን፣ አልባሳትን ወዘተ.../ ማድረግ፣
- ከፍተኛ የሆነ የምግብ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች ሕብረተሰቡ በምግብ ራሱን እንዲችል ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ የትምህርት ቤት ምገባ ኘሮግራም ጠባቂነትን በማያስፋፋ መልኩ ማካሄድ፣
- የጎሣ ግጭቶችን መፍታት፣ ሰላምን በዘላቂነት ለማስፈን የሚያስችል ትምህርት (peace education) ለሕብረተሰቡ መስጠት፣

### 3.1.2 የአማራጭና የመደበኛ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ጥራትና ተገቢነት ማሻሻል

- ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርትና ለመደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የሚዘጋጁ የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍት ከአርብቶአደሩ አኗኗርና ሕይወት ጋር የተገናዘቡና ለወቅታዊ ሁኔታዎች ትኩረት የሚሰጡ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በአካባቢው የሚዘጋጁ የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍትን ሞጁላርና self-instructional በሆነ መንገድ ማዘጋጀት፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች ተማሪዎችን በማሳተፍ የመሥራት ባህልን ማዳበር፣
- የመማሪያ ማስተማሪያ መፃሕፍትን በየወቅቱ በባለሙያ ማስገምገምና ማሻሻል፣ እንዲሁም በተቻለ መጠን የመጽሐፍ ተማሪ ጥመርታን 1፡1 ማድረግ፣

- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አመቻቾችንና የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንን ሙያዊ ብቃት ተከታታይ በሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና ማሳደግ፣
- አመቻቾች በርቀት ትምህርት አማካኝነት የትምህርት ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁም በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት/ኮሌጆች ተመዝግበው በተቀናጀ የክረምት የገፅ ለገፅ ስልጠናና በበጋ የርቀት ትምህርት ፕሮግርራም አማካኝነት በሰርፊኬት እንዲመረቁና ወደ መደበኛ መምህርነት እንዲሸጋገሩ ማድረግ፣
- የመማር-ማስተማሩን ሂደት አሣታፊና ተማሪ-ተኮር ማድረግ፣
- የአካባቢ ባለሙያዎችን፣ ታዋቂ ግለሰቦችንና የማህበረሰብ መሪዎችን በመማር ማስተማሩ ሂደት በማሳተፍ የተካበተ ልምዳቸውን ለተማሪዎች እንዲያካፍሉ ማድረግ፣
- የትምህርት ጥራትን ከፍ ለማድረግ፣ ሪሶርስን በጋራ ለመጠቀምና የአመቻቹን ብቃት በተከታታይነት ለማጎልበት የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ከመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ጋር ማጎዳኘት፣ /በክላስተር ማቀናጀት/ የተጠናከረ የመረጃ ሥርዓት በቀበሌ ደረጃ እንዲኖር ማድረግ፣ የፍሰት ሥርዓት መዘርጋት፣
- በተመሳሳይ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችን እርስ በራሳቸው ማጎዳኘት፣
- በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችና የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች በአካል በመገኘት የታቀደና በቂ ሱፐርቪ¡ን አገልግሎት መስጠት ማድረግ፣ በተለይ አመቻቾች ካላቸው ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃና የአጭር ጊዜ ስልጠና አንፃር የድጋፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ልዩ ትኩረት መስጠት፣

### 3.1.3 በክልል፣ በወረዳና በት/ቤት (ጣቢያ) ደረጃ የትምህርት ዕቅድና አመራርን ማሻሻል

#### 3.1.3.1 የሰው ሀብትን ማልማት (አቅም መገንባት)

- የክልል ትምህርት ቢሮና የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊዎችንና ባለሙያዎችን አቅም በተሞክሮ መቅሰሚያ ትምህርታዊ ጉብኝቶች፣ በልምድ ልውውጥ መድረኮችና ተከታታይነት ባላቸው የሙያ ልማት ስልጠናዎች አማካኝነት ማጎልበት፣
- የተልዕኮና የርቀት ትምህርት ዕድሎችን መክፈት በሩቅ አካባቢ የሚኖረው የሕብረተሰብ ክፍል በዕድሎቹ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስልት መቀየስ፣

- የፖለቲካ ተሹዋሚዎች በዝቅተኛ ደረጃ ማሟላት የሚገባቸውን የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ መወሰን የተወሰነ ካለም ተግባራዊ ማድረግ፣
- በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚታየውን የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ ከሌሎች ክልሎች የተመለመሉ የትምህርት ፐርሶኔሎችንና የተባበሩ መንግሥታት በጎ ፈቃደኞችን በጊዜያዊ መፍትሄነት መጠቀም፣

3.1.3.2 በዚህ ሰነድ ውስጥ የተካተቱ ስልቶችን መሠረት በማድረግ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በ2008 ዓ.ም. ለሁሉም ሕፃናት ለማዳረስ የተጣለውን የምዕተ ዓመቱን የልማት ግብ በአርብቶ አደር ክልሎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መሪ ዕቅድ (master plan) በክልል፣ በወረዳና በአካባቢ ደረጃ ማዘጋጀትና በተግባር መተርጎም፣

3.1.3.3 የወረዳና ቀበሌ ልማት ኮሚቴዎችን እንዲሁም የመደበኛ ት/ቤትና የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ ትምህርት አመራር ኮሚቴዎች የማቀድና አመራር የመስጠት አቅም መገንባት፣

3.1.3.4 ት/ቤቶችን (ትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን) በአስፈላጊ የትምህርት ቁሳቁሶችና ፋሲሊቲዎች ማሟላት፣

3.1.3.5 ለክትትል፣ ግምገማና ለሱፐርቪ ¡ን ድጋፍ አስፈላጊ የሆኑ የትራንስፖርት ፋሲሊቲዎችን ማሟላት፣

3.1.3.6 በክልልና በወረዳ ደረጃ ያለውን አስተዳደር ለማሻሻል፡-

- በክልል ት/ቢሮና ሌሎች ሴክተር ቢሮዎች፣ በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤትና በሌሎች ሴክተር ጽ/ቤቶችና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለው ግንኙነት በመተማመንና በግልፅነትት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ፣
- በመልካም አስተዳደር ላይ ሥልጠና መስጠት፣
- ህብረተሰቡ በትምህርት ሥራ እቅድ፣ በትምህርት ቤትና በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ ግንባታና በአመራር ላይ ንቁ ተሳትፎና የባለቤትነት ስሜት እንዲኖረው ማድረግ፣ በክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ማሳተፍ ለዚህም በየደረጃው ላሉ

የህብረተሰቡ አመራር አካላት የገንዘቤ ማዳበሪያና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ተከታታይነት ባለው መልክ ማከናወን፣

3.1.3.7 የትምህርት በጀትን በተመለከተ፡-

- ለአርብቶ አደር ክልሎች የሚመደበውን የትምህርት በጀት ማሳደግ፣
- ከደመወዝ ውጪ ያለው መደበኛ የትምህርት በጀት በአብዛኛው ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ለሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት፣ ለሥልጠናና ሱፐርቪ ¡ ን አገልግሎት እንዲውል ማድረግ፣
- ለትምህርት ሥራ የተመደበው የትምህርት በጀት በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣

## 3.2 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

- ከዓመት ዓመት እያደገ የሚሄደውን የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ፍላጎት ለማስተናገድ ተጨማሪ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን በሕብረተሰቡ ተሣትፎ መገንባት፣
- 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን እንደ ቤተመፃሕፍት ላቦራቶሪ ባሉ ፋሲሊቲዎችና አስፈላጊ የትምህርት መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ማሟላት፣
- በተበታተነ አሰፋፈር የሚኖሩ የአርብቶ አደር ልጆች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ አማካይ በሆነ ቦታ በአነስተኛ ወጪና በህብረተሰብ ተሣትፎ አዳሪ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ማቋቋም፣
- በተመሳሳይ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ባለባቸው አካባቢዎች የሆስቴል አገልግሎትን በማደራጀት ከሩቅ አካባቢ የሚመጡ ተማሪዎችን ማስተናገድ፣
- አዳሪ ት/ቤቶቹ የውስጥ ገቢ የሚያመነጩበትንና ወጪን የሚጋሩበትን ስልት መቀየስ፣
- በአካባቢያቸው የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል /5-8/ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የማያገኙና በባሰ ደህነት ውስጥ የሚኖሩ ተማሪዎች ትምህርት ቤት በተቋቋመበት አካባቢ ከዘመድ ጋር ተጠግተው መማር እንዲችሉ ለቀለብና ለአልባሳት የሚሆን የኪስ ገንዘብ እየሰጡ ማስተማር፣
- የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ጥራትና ተገቢነት ለማሻሻል
  - ICT (Information Communication Technology)ን ከአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ መጠቀም፣

- የ2ኛ ደረጃ መምህራንን አቅም ተከታታይ በሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና መገንባት፣
- ለደረጃው የሚመጥኑ መምህራንን በበቂ ቁጥር መመደብና በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ ማድረግ፣

- ጥራቱን የጠበቀ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመስጠት በወረዳ/በዞን ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በማጎዳኘት መምህራን በየትምህርት ዓይነቱ /በዲፓርትመንት/ ልምድ የሚለዋወጡበትንና ሪሶረስን በጋራ የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ ለዚህም ሪሶርስ ማዕከላትን ማቋቋምና ማጠናከር፣ በሀገሪቱ የተሻለ ከሚሰሩ ት/ቤቶች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚቀስሙበትን መንገድ ማመቻቸት፣

## 3.3 የርቀት ትምህርት

- በተለያዩ ምክንያቶች መደበኛ ትምህርት ቤት መግባት ላልቻሉ ወይም ትምህርት ጀምረው ላቋረጡ ወጣቶች የቤት እመቤቶች ጎልማሶች ወዘተ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል /5-8/ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት በርቀት የማስተማሪያ ዘዴ ትምህርት እንዲከታተሉ ማድረግ፣ ለዚህም የቲቶሪያል አገልግሎትና self learning or modular የትምህርት ማሳሪያዎች ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ማዋል።
- በተለይም በአርብቶአደር ክልሎች በሚካሄደው የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም በአመቻችነት ተመድበው በማገልገል ላይ የሚገኙ ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸውን ወጣቶችን በርቀት ትምህርት እንዲያሻሽሉና ሌሎች አቅም ግምባታ ፕሮግራሞችን እንዲያገኙ ማድረግ።

## 3.4 የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና

- በክልሎቹ ያሉ የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጆች ከመደበኛ ሥልጠና ባሻገር የአካባቢውን አቅም በማጎልበት ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ማሰልጠኛ ተቋማቱ ከመደበኛ መምህራን ሥልጠና ጎን ለጎን ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አመቻቾች ሥልጠና የሚሰጡበትን አደረጃጀት መፍጠር፣

- የአሠልጣኝ መምህራንን አቅም ከሌሎች ተቋማት ጋር ቁርኝት በመፍጠርና በልምድ ልውውጥ ማጎልበት፣
- በአርብቶ አደር ክልሎች የሚገኙ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት በሚሰጡት የመደበኛ መምህራን ሥልጠና ውስጥ ስለአርብቶ አደሩ አኗኗርና ባሕል ኮርሶችን እንዲሰጡ ማድረግ፣
- ወደ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት የሚገቡ ሰልጣኞች መግቢያ መመልመያ መስፈርቶች የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፣ /ቢቻል 1ኛ ደረጃን ያጠናቀቁና ከዚያም በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸውን መቀበልና ቅድማያ ለሴቶች መስጠት/፣
- በክልልና ወረዳ ደረጃ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል ለሚያደርጉ ባለሙያዎች ተከታታይነት ያለው የሱፐርቪዥን ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በተቋማቱ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በአርብቶአደሩ ሕይወት ላይ ለውጥ የሚያመጡና በአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የመምህራን አቅም በዘላቂነት ለመገንባት ተከታታይ የሆኑ የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና የመምህራንን ደረጃ ማለትም ከሠርቲፊኬት ወደ ዲፕሎማ፣ ከዲፕሎማ ወደ መጀመሪያ ዲግሪ ወዘተ ለማሳደግ የሚያስችሉ የሥልጠና ፕሮግራሞችን ማመቻቸት፣
- በመምህራን ልማት መርሃ ግብር (TDP) ሰነድ ውስጥ የተቀመጡት ዓላማዎች ማለትም፣
  - ተገቢው አካዳሚያዊ ዕውቀት፤ ሙያዊ ሥነ ምግባርና አወንታዊ አመለካከት ያላቸው፤ ለሙያቸው ቁርጠኛ የሆኑና በራሳቸው የሚተማመኑ፤ ተማሪዎችን በማሳተፍ ተግባራዊ ምርምርን የሚያከናውኑ፤ ተከታታይ ምዘናና ግምገማን እንዲሁም በክፍል ውስጥ የዴሞክራሲ መርሆዎችን ሥራ ላይ የሚያውሉ፣
  - ስለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች በቂ ዕውቀት ያላቸውና ተማሪዎቻቸውን እንደአስፈላጊነቱ የሚያግዙ መምህራንን በተለይም ሴት መምህራንን በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለማፍራት አስፈላጊውን የተግባር እንቅስቃሴ ማድረግ።

## 3.5 መደበኛ ያልሆነ የጎልማሶች ትምህርት

- በፌዴራል ደረጃ የተዘጋጀውን የጎልማሶች ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ ከአርብቶአደሩ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ክልላዊ ስትራቴጂ መንደፍና ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ፣
- በአርብቶአደሩ ላይ ጐልቶ የሚታየውን ድህነት ለመቀነስ ይቻል ዘንድ ከአርብቶአደሩ ዕለት ከዕለት ሕይወትና መተዳደሪያ ጋር የተጎዳኙ የfunctional literacyና ሌሎች መደበኛ ያልሆኑ የጎልማሶች ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ተግባራዊ ማድረግ ለዚህም: አግባብ ካላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ አጋር ድርጅቶች ጋር ተቀናጅቶና ሃብትን አሰባስቦ መስራት የሚቻልበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

## 3.6 የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ማስቀረት

- ቤተሰብና ሕብረተሰቡ በአጠቃላይ የሕፃናትን ጉልበት ብዝበዛ አስከፊነት እንዲገነዘብና የሕፃናት ጉልበት በዝባዦች ሰለባ እንዳይሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫና የአሕዝቦት ሥራ ማከናወን፣
- ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አመቻቾችና መደበኛ መምህራን በሚሰጡ ሥልጠ ናዎች ውስጥ ስለ ሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ አስከፊነትና ጉዳት እንዲ ካተት ማድረግ፣
- በሕፃናት ላይ ያለውን የጉልበት ሥራ ጫና ለመቀነስ አርብቶአደሩ ተሰባስቦ በሚኖርባቸው ቦታዎች ሁሉ የመንደር ት/ቤቶችን ማቋቋም፣
- በአርብቶአደር አካባቢ የሚገኙ ሕግ አስፈጻሚ አካላት የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን መከላከል እንዲችሉ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥራዎችን ማከናወን፣

## 3.7 የሬዲዮ ትምህርትን በስፋት መጠቀም

- የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክልንና የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አመቻ ቾችን፣ መደበኛ ያልሆነ የጐልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞችንና የአሕዝቦት ሥራ

ዎች ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራሞች በሰፊው እንዲደገፉ ማድረግ፣ በተለይም በዝቅተኛ ወጪ ሊገነቡ የሚችሉ የአካባቢ ሬድዮ ጣቢያዎችን (FM) ማቋቋምና ለትምህርቱ ሥራ መጠቀም፣

- ሌሎች የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ /ICT/ መሳሪያዎችን እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ መጠቀም፣

## 3.8 በየደረጃው ላሉ መምህራን ባለሙያዎች ልዩ የማትጊያ ስልት መንደፍ

- ለኑሮና ለጤና አስቸጋሪ በሆኑት የአርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚሰሩ መምህራንና ባለሙያዎች ልዩ ልዩ የማበረታቻ ድጋፎችን ማድረግ፣ ለዚህም የሌሎች አካባቢዎችንና ሀገሮችን ተሞክሮዎች መውሰድ፣ የተገኙ ለውጦችን በየጊዜው ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣

## 3.9 ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ

- በአርብቶአደር ክልሎች በየደረጃው የሚከናወኑ የትምህርት ተግባራት በየሩብ ዓመቱ የሚገመግም የክልልና የማዕከል አስፈጻሚ አካላትን ያሳተፈ የምክክር ጉባኤ ማካሄድ፣
- በየ6 ወሩ የክልል፣ የወረዳና  የማዕከል የትምህርት አመራር አካላት የሚገኙበት የልምድ ልውውጥና ግምገማ መድረክ ማዘጋጀት፣
- የትምህርት መረጃ ፍሰት ሥርዓት በየደረጃው መዘርጋትና መረጃ ማሰባሰብ፣ የሩብ ዓመት፣ የ6 ወርና የዓመት ሪፖርት ማጠናቀርና ለዓመታዊ የትምህርት ጉባኤ ማቅረብ፣
- በየደረጃው ያሉ የአስፈጻሚ አካላት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ያካተተ የሥራ ድርሻ እና ሃላፊነት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- በአርብቶ አደር ክልሎች ተጨባጭ የሆኑ አካባቢያዊ ለውጦች እስኪመጡ ድረስ ከማዕከል የሚሰጠውን የክትትልና ግምገማ ሥርዓት አጠናክሮ መቀጠል። እስካሁን በመሰጠት ላይ ያለው ልዩ ድጋፍም ከክልሎች ፍላጎቶች ጋር በማጣጣምና በጋራ በማቀድ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ፣

- ለአቅም ግንባታ ሥልጠና ከአርብቶ አደር ክልሎች የሚመጡ ባለሙያዎችና ሃላፊዎች የሠለጠኑበትን ለሌሎች ማካፈላቸውን ትኩረት ሰጥቶ መከታተልና ድጋፍ ማድረግ፣
- ሕብረተሰቡ በተለይም ወላጆች በትምህርት መስጫ ጣቢያ ደረጃ በትምህርቱ
- ሥራ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ላይ ክትትልና ግምገማ የሚያደርጉበትን ሥርዓት-መዘርጋት፣

## 3.10 ትስስርና አጋርነት

- ትምህርት ሚኒስቴር በትምህርቱ ዘርፍ ለአርብቶአደር ክልሎች በመስጠት ላይ ያለውን ልዩ ድጋፍ አጠናክሮ በመቀጠል ክልሎቹን የማብቃት ሥራ መሥራት፣ በአርብቶአደሩ ልማት ድርሻ ካላቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት መ/ቤቶች በተለይ ከጤና ፣ውሃ እና የምግብ ዋስትና መስሪያ ቤቶች ጋር በየደረጃው በፌደራል፣በክልልና በወረዳ ደረጃ በቅንጅት መሥራት፣የተሰሩ ሥዎችንም በየወቅቱ በጋራ መገምገም፡፡
- በአርብቶአደሩ ትምህርት ላይ ከተሰማሩ ዓለምአቀፍና አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር Partnership እና Networking መፍጠር፣ የተጀመሩትንም ማጠናከር፣
- ዩኒቨርሲቲዎች በተለይም በአርብቶአደሩ ክልሎች የሚቋቋሙ ዩኒቨርሲቲዎች የአርብቶአደሩን ትምህርትና ሥልጠና ለማጠናከር በሚያስችሉ የጥናትና ምርምር፣ የአቅም ግንባታ ወዘተ ሥራዎች በመሳተፍ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣
- በአርብቶአደርና በአጎራባች ክልሎች መካከል የተጠናከረ ግንኙነት በመፍጠር የአንደኛ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትና መምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት በአጋርነት የመሥራት ባህልን ማዳበርና አርብቶ አደር ክልሎች እራሳቸውን እንዲያበቁ ማገዝ፣
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂን በየደረጃው ተግባራዊ ለማድረግ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊና መያዶች እንዲሁም ከሕብረተሰቡ ጋር በጋር መሥራት፣

## 3.11 የአስፈጻሚ አካላት ተግባርና ሃላፊነት

ሀ. የፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ሃላፊነትና ተግባር፣

በአዋጅ የተሰጡት ሃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

- ከአርብቶ አደር ክልሎች ጋር በመመካከርና በክልሎቹ ፍላጎቶች ላይ በመመሥረት የልዩ ድጋፍ ዕቅድ በጋራ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ።
- የአርብቶ አደር ክልል የትምህርት አመራር አካላትና ባለሙያዎችን ትኩረት ሰጥቶ አቅማቸውን በተከታታይ መገንባት፡ ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት።
- ለአርብቶ አደር ትምህርት ልማት እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ ሀብት ማፈላለግ።
- ለአርብቶአደሩ ትምህርት ድጋፍ በሀላፊነትና በባለሙያነት የሚመደቡ ሰዎችን የቁርጠኝነት ስሜት ማሳደግ፣
- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ትምህርትን በጥራት ለማስፋፋት የሚረዱ አዳዲስ አሠራር ሥልቶችን ከሌሎች አገሮች ተሞክሮዎችና በአካባቢው ከሚካሄደው የጥናት ግኝቶች ላይ በመመሥረት ሥራ ላይ ማዋል።

ለ. የክልል ት/ቢሮ ሃላፊነትና ተግባር፣

የአርብቶ አደር ክልል ትምህርት ቢሮዎች በአዋጅ ከተሰጣቸው ሃላፊነት በተጨማሪ ለአርብቶ አደሩ ትምህርት መስፋፋትና ጥራት መጠበቅ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ።

- የትምህርት ፖሊሲውንና የአርብቶአደሩን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት በማዘጋጀት ሥራ ላይ ማዋል፣
- በየደረጃው የሚቀመጡ የትምህርት አስፈጻሚ አካላት ለአርብቶአደሩ ትምህርት በቁርጠኝነት መሰለፋቸውን ማረጋገጥ፣
- ለወረዳዎች የማቴሪያል፣ የሙያና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግና የባለሙያና የትምህርት አመራር አካላትን አቅም መገንባት፣
- ለአርብቶአደሩ ትምህርትና ሥልጠና ውጤታማነት፣ አጋር የሆኑ መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና ሕዝባዊ ተቋማትን ማስተባበርና መከታተል፣

- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርትን መንደፍ የመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍትን ማዘጋጀት፣ ማሳተምና ማሠራጨት፣
- ለአመቻቾች የቅድመ ሥራና ተከታታይ የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት፣
- መምህራን ወደ ሥራው እንዲመጡና በሥራው ላይ እንዲቆዩ ልዩ ልዩ የማበረታቻ ስልቶችን መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ፣
- ከማዕከል የሚያስፈልጋቸውን ልዩ ድጋፍ ማንጠርና ማሳወቅ፣

ሐ. የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊነትና ተግባር

- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን፣ ት/ቤቶችንና፣ ፓራ ቦርዲንግ ሆስቴሎችን ህብረተሰቡን በማሳተፍ መገንባትና ማስተዳደር፣
- በወረዳ ውስጥ የአርብቶአደር ትምህርትና ሥልጠና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ የሚስፋፋበትን በተለይም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም የሚዳረስበትን ስልት መቀየስ፣ ተግባራዊ ማድረግና አፈጻጸሙን መከታተል፣
- ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የተጠናከረ የሱፐርቪዥን አገልግሎት መስጠት፣ ለዚህም አስፈላጊውን የትራንስፖርት አገልግሎትና በጀት በወረዳ ደረጃ መመደብ፡፡
- በወረዳ ለሚገኙ አመቻቾች፣ ተከታታይነት ያላቸው ሥልጠናዎችንና የልምድ ልውውጦችን ማዘጋጀት፣
- በወረዳው ውስጥ የሚገኙ መምህራንና ባለሙያዎች በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ የተለያዩ የማትጊያ ስልቶችን መንደፍ፣ ተግባራዊ ማድረግና መከታተል፣
- በአርብቶአደሩ ትምህርትና ሥልጠና ላይ ሕብረተሰቡ በባቤትነት ስሜት እንዲሳተፍ ተከታታይ የግንዛቤ ማዳበሪያና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በማከናወን፣ በትምህርት ተቋማት ግንባታና በትምህርት መሣሪያዎች አቅርቦት በጉልበቱ፣ በእውቀቱና በገንዘቡ ተሳትፎ የሚያደርግባቸውን ስልቶች መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በወረዳ ደረጃ በትምህርት ሥራ ከተሰማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና አጋር ከሆኑ መንግሥታዊ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት መሥራት፣
- በወረዳው ያሉትን የሌሎች ዘርፍ ሠራተኞች ምሁራዊ አቅማቸውን ለትምህርት እንዲያውሉ ማበረታታትና ማስተባበር፣

- በወረዳው ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በየጊዜው መፈተሽ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን መለየት፣ ድጋፎችን ተግባራዊ ማድረግ የተግባር መመሪያ ማዘጋጀት፣ ተግባራዊነቱን መከታተል፣

መ. የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት /ኮሌጅ/ ኃላፊነትና ተግባር

የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ከተሰጣቸው የሥራ ድርሻ በተጨማሪ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ፦

- በተቋማቸው ውስጥ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ዩኒት /ዲፓርትመንት በማቋቋም የአመቻቾችን ሥልጠና የሥራቸው አካል ያደርጋሉ፣
- በመደበኛና የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍት ዝግጅት ይሳተፋሉ፡፡
- ያሰለጠኗቸውን አመቻቾች/ መምህራን በመስክ በመገኘት ይገመግማሉ። ከግምገማው በሚያገኙት ግብረ-መልስ መሠረትም ድክመቶች የሚቃለሉበትንና የወደፊት ስልጠናዎች ተጠናክረው የሚሰጡበትን ሥልት ይቀይሳሉ፡፡
- በየወቅቱ ለመደበኛና አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የተዘጋጁትን መጽሐፍት ብቃት ይገመግማሉ፡፡
- የአመቻቾችን ትምህርት ደረጃና የሙያ ብቃት ለማሳደግ አጫጭርና የረጅም ጊዜ ሥልጠናዎችን በማዘጋጀት አመቻቾችን የሰለጠኑ መምህራን /certified Teachers/ ያደርጋሉ፡፡

ሠ. ሌሎች አካላት እንደ አስፈላጊነቱ በትምህርቱ ሥራ ላይ ይተባበራሉ።